# የአርበኞች ግንቦት 7 ድምጽ

የአርበኞች ግንቦት 7፣ ለአንድነትና ዲሞክራሲ ንቅናቄ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

የአርበኞች ግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 355 የካቲት 21 2007 ገጽ

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

አርበኞች ግንቦት 7: የአንድነትና ዲሞክራሲ ንቅናቄ የኢትዮጵያ የመከላከያና የፓሊስ ሠራዊት አባላት ለራሳቸው እና ለወገናቸው የሚበጀው ሥርዓት የቱ እንደሆነ ያውቃሉ ብሎ ያምናል። በዚህም ምክንያት ስብዕናቸውን እያዋረደ እና እያደኸያቸው ያለውን የህወሓት አገዛዝን ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር በመሆን ይፋለሙታል ብሎ ያምናል።

ከአርበኞች ግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የግንቦት 7ና የአርበኞች ግንባር መዋሃድ በፋሽስቱ ወያኔ መንደር ከፍተኛ አለመረጋጋት እንደፈጠረ ነዉ

ዘረኛውንና ከፋፋዩን የወያኔ አገዛዝ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጫንቃ ለማውረድና የኢትዮጵያንና የህዝቦቿን ትንሳኤ ለማፋጠን በጋራ ለመታገል የቆረጡት የግንቦት 7 ንቅናቄና አርበኞች ግንባር ታሪካዊ የተባለለትን ውህደት መፈጸማቸው የሚታወቅ ሲሆን ውህደቱን ተከትሎ በወያኔ መንደር የተፈጠረው አለመረጋጋት ተባብሶ መቀጠሉን የውስጥ ምንጮቻችን አመለከቱ። በውህደቱ እንቅልፍ ያጡት የህወሃት ቱባ ሹማምንት በተለይ በመላ ሀገሪቱ የሚገኙ ካድሬዎቻቸውን ከፍተኛ ጥበቃ እንዲያደርጉ ለመሸንገልና ለመማጸን በየክልሉ አስቸኳይ ስብሰባ ለማድረግ ቅደመ ዝግጅት ማጠናቀቃቸው ለማወቅ የተቻለ ሲሆን ስልጠናው በዋናነት የአርበኞች ግንቦት 7 ዉህደትን የተመለከተ እንደሆነ ተመልክቷል።

በተያያዘ ዜና ውህደቱን ተከትሎ በአማራ ክልል በተፈጠረው ህዝባዊ መነቃቃት የተደናበሩት የጉጅሌው ቱባ ሹማምንት በአማራ ክልል ብአዴን የወጣቶች ዘርፍ መምሪያ በኩል በክልሉ ላሉ ለ 11 ዞን ተወካዮች አስቸኳይ መልዕክት የተላለፈ ሲሆን በተለይም አባሎቻቸዉ በፌስቡክ ከተሰጣቸዉ ተልዕኮ ዉጭ በኢሳትና በተቃዋሚ የፓለቲካ ድርጅቶች ድህረ ገጽ የሚለቀቁ ቪዲዮችን እንዳይመለከቱ ጥብቅ ትእዛዝ ተላልፎል። ሌላዉ የአርበኞች ግንቦት 7 ንቅናቄ ሊቀመንበር በሆኑት ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ከሰሞኑ በሰጡት ቃለ ምልልስ ላይ ያተኮረ የመልስ ምት ዘመቻ የ 5 ለ 1 አባላት የሶሻል ሚዲያ ኮሚቴዎች የትኩረት አቅጣጫ እንዲሆን ከብአዴን ፅ/ቤትና ወጣቶች ማደራጃ ክፍል ሰርኩሌት መደረጉንም ለማወቅ ችለናል። ...... ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## በወልቃይት ጠገዴ አንዣቦ የሚገኘው ህዝባዊ አመጽ ሊፈነዳ መቃረቡን ምንጮች ጠቆሙ

የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ በወልቃይት ጠገሌ ያንሰራፋው የመልካም አስተዳደር እጦትና ስርአት አልበኝነት የወለደው እንደሆነ እየተነገረለት የሚገኘው ህዝባዊ አመጽ ከቁጥጥር ውጭ እየወጣ በመሄዱና ሊፈነዳ በመቃረቡ የአገዛዙ ቅጥረኛ ሹማምንት ከፍተኛ ውጥረት ውስጥ መግባታቸውን ከወደ አካባቢው የደረሰን ዜና አመለከተ። በተለይ የህዝባዊ አመጹ መነሻ ከአርሶ አደሮች መንደር ማለትም በወረዳዎቹ ገጠራማ ቦታዎች ላይ ሊሆን እንደሚችል በስፋት እየተነገረ ሲሆን ለዚህም ዋነኛ ምክንያቱ ዘረኛው የህወሓት አገዛዝ በብዙ አስር ሺዎች የሚገመቱ አርሶ አደሮችን ህጋዊ መሬቶቻቸውን በመንጠቅ በልማት ስም የትግራይ ተወላጅ ለሆኑ ቅጥረኛ ባለሃብቶች በማከፋፈሉ እንደሆነ የተመለከተ ሲሆን መሬቶቻቸው የተነጠቁባቸው አርሶ አደሮች ለአመታት አቤቱታ ቢያቅርቡም ሰሚ በማጣታቸው ለከፍተኛ ስቃይና እንግልት ተዳርገው የችግር ህይዎት እንዲገፉ መገደዳቸውን ለማወቅ ችለናል። ...... ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## በአዋሳ ከተማ አዲሱ ገበያ እየተባለ የሚጠራው ሰፈር ሙሉ ለሙሉ በእሳት ወደመ

ቅዳሜ ምሽት በአዋሳ ከተማ አዲሱ ገበያ እየተባለ በሚጠራው ሰፈር በደረሰው የእሳት አደጋ ከ 7 የማያንሱ ሰዎች መሞታቸውንና ከ23 በላይ የሚሆኑት ደግሞ ቃጠሎ ደርሶባቸው የተጎዱ መኖራቸውን ምንጮቻችን አመለከቱ። የእሳቱን መንስኤ በውል ለማወቅ ያደረግነው ጥረት እስካሁን ባይሳካም አንዳንድ የአካባቢው ነዋሪዎች ግን አደጋው ሆን ተብሎ በዘራፊው የወያኔ አገዛዝ የተፈጠረ የጥፋት ሴራ እንደሆነ አስረግጠው ተናግረዋል። የእሳት አደጋው ከተነሳ በኋላ በቦታው የደረሱት የእሳት አደጋ ሰራተኞች እሳቱን ለማጥፋት አፋጣኝ እርምጃ ለመውሰድ አለመፍቀዳቸው የአካባቢውን ነዋሪዎች ክፉኛ ማስቆጣቱን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን በህዝቡና በሰአቱ በጣለው ከፍተኛ ዝናብ እሳቱ ሊጠፋ መቻሉ ታውቋል። በአደጋው ንብረቶቻቸው ሙሉ በሙሉ የወደመባቸው ሰዎች ቁጥር ከ 800 በላይ እንደሆነ ታውቋል።.

..... ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

ግዜ ግንቦት 7 ዜና

## አባይ ፀሀዬ የአዲስ አበባን ማስተር ፕላን በኃይል እንተገብራለን ብሎ መዛቱ ዉጤቱ ኣመጽ ብቻ ነዉ -ሂውማን ራይትስ ሊግ

"ልክ እናስገባቸዋለን!" ከሰሞኑ የጉጅሌው ወያኔ ቅጥረኛ የሆነው አባይ ጸሐየ ለኦሮምያ ክልል ህዝብ ያለውን ከፍተኛ ንቀትና ጥላቻ የገለጸበት አስጸያፊ የዛቻ ቃል ሲሆን ከዚህ ጋር በተያያዘ የወያኔው ቱልቱላ አባይ ጸሃየ በክልሉ ህዝብ ላይ የሰነዘረው ንቀትና ዛቻ ተጨማሪ ደም መፋሰስ ሊያስከትል እንደሚችል ሂውማን ራይትስ ሊግ ከወዲሁ ስጋቱን ገልጿል።

ከአዲስ አበባ ማስተር ፕላን ጋር ተያይዞ በፋሽስታዊው አገዛዝ ታቅዶ የነበረው የመሬት ዘረፋ ከፍተኛ ደም መፋሰስ አስከትሎ መቋረጡ የሚታወስ ሲሆን ከሰሞኑ የጉጅሌው ቱልቱላ አባይ ጸሐየ የመሬት ዘረፋውን በድጋሚ በሃይል እንደሚተገበር ለማድረግ ዝግጅት መጠናቀቁን ተናግሯል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ የሰብአዊ መብት ሊጉ ባወጣው መግለጫ ድርጊቱ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ አመጽን የሚጋብዝ ብቻ ሳይሆን፤ ከዚህ ቀደም የደረሰው ደም መፋሰስ ሳይበቃ ተጨማሪ ደም መፋሰስ እንዲኖር የሚጋብዝና የሰው ህይወት እንዲጠፋ የሚያደርግ ነው ሲል እርምጃውን አውግዟል። የቱልቱላው አባይ ጸሃየ እብሪት የተሞላበት ንግግር ለውይይት፤ ለምክክር እንዲሁም ለዜጎች ይሁንታ ቦታ የማይሰጥ በመሆኑ አደኛ ነው ሲልም መግለጫው አትቷል።

...... ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## የወያኔ ፋሽስቶች ወያኔ የተማረውን ኢትዮጵያዊ በፍጹም እንደማያምኑ የተናገሩት ንግግር ይፋ ሆነ

በስልጠና ስም ዜጎችን አደንቁሮ ለመግዛት የሚባዝነው የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ ከሰሞኑ ለአገዛዙ ከፍተኛ ቅጥረኞች ስልጠና ባዘጋጀው ሰነድ ላይ፤ በአገዛዙ ተቋማት ውስጥ ተቀጥረው እየሰሩ የሚገኙትን የተማረው ክፍል በፋሺስታዊው አገዛዝ የመጨረሻው የማይታመነው ክፍል ነው ሲል ገልጾታል። "ይህ የተማረው ሃይል" ይላል ሰነዱ "ህዝባዊ አመፅ የመምራት፤ ኢሳትና ቪኦኤን ከመሳሰሉ አፍራሽ ሚዲያዎች ጋር በመተባበር የቀለም አብዮት ለመምራት ፣ አመጽ ለማደራጀት እና መሪ ተዋናይ ለመሆን ያለው እድል ሰፊ ነው" ሲል ገልጿል።

የተማረው የመንግስት ሰራተኛ "ለውጥ ፋላጊ ፣የመረጃ ሃይል እና አቅርቦት በተደራጀ አግባብ ያለው፣ እራሱን እንደሚዛናዊ ሃይል የሚቆጥር እና በበደሉት ጥቂት አመራሮች ላይ አቂሞ የሚገኝ "እንዲሁም ሌላውንም የማስካድ አቅም ያለው በኢህአዴግ የመጨረሻው የማይታመነው ክፍል ነው ተብሎ በኢህአዴግ መፈረጁንም ሰነዱ ይገልጻል። የመንግስት ሰራተኛው ልማታዊ አልሆነም የሚለው የስለጠና ሰነዱ፣ ይህንኑ ለመፈጸም በአምስት ክፍሎች የተዋቀረ የለውጥ ሰራዊት አደረጃጀት መዘጋጀቱንም ይናገራል። አንደኛው እና የለውጥ ሰራዊቱን የበላይ ሆኖ የሚቆጣጠረው ኮማንድ ፖስት የሚባለው ክፍል ሲሆን፣ በዚህ እዝ ስር ሚኒስትሮችና የተቋማት ስራ አስፈጻሚዎች መካተታቸውን ይናገራል። ሁለተኛው የስልጣን ክፍል ደግሞ ፕሮሰስ ካውንስል የሚባለው ሲሆን፣ በዚህ ክፍል የተቋም ሃላፊዎች ፣ የስራ ሂደት ሃላፊዎች ተመድበዋል። የስራ ሂደት በሚባለው ሶስተኛው ክፍል ደግሞ የስራ ሂደት ሃላፊና የቡድን ሃላፊዎች ተካተውበታል። ...... ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## አብዛኞቹ የመንግሰት ጋዜጠኞች የኢህአዴግ አባላት መሆናቸውን መረጃዎች አመለከቱ

በመንግስት የመገናኛ ብዙሃን ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩ ጋዜጠኞች አብዛኞቹ የኢህአዴግ አባላት መሆናቸውን ኢሳት በደረሰው የአባላት ስም ዝርዝርና የስራ ድርሻ ሰነድ ለማረጋገጥ ችሎአል። በቀድሞው ኢቲቪ በአዲሱ አጠራሩ ኢቢሲ እና በኢትዮጵያ ሬዲዮ ስር የሚሰሩ ዳይሬክተሮች፣ የዜና አዘጋጆች፣ የወቅታዊ ዘገባ አቀናባሪዎች፣ የስፖርት ጋዜጠኞች ፣ የካሜራ ባለሙያዎች፣ ቴክኒሻኖችና የተለያዩ የድጋፍ ሰራተኞች የህወሃት፣ የብአዴን፣ ኢህዴድ ወይም የደህዴግ አባላት መሆናቸው በሰነዱ ላይ በዝርዝር ተቀምጧል። ጋዜጠኞቹ የኢህአዴግን ፖሊስ ለህዝብ ከማስተዋወቅ ጋር በተያያዘ በየጊዜው በተደራጁበት ህዋስ ስር ግምገማ እንደሚደረግባቸውና ከኤ እስከ ዲ የሚደርስ ውጤት እንደሚሰጣቸው ከሰነዱ ለመራዳት ይቻላል።

የመንግስት የመገናኛ ብዙሃን በህዝብ ንብረት የሚተዳዳሩ ቢሆንም፣ የአንድ ፓርቲ አገልጋይ ለመሆናቸው ከዚህ በላይ ...... ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## ምርጫ ለኢትዮጵያ ወታደርና ፓሊስ: - ለህወሓት ባርነት ወይስ ለኢትዮጵያ ነፃነት?

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለውትድርና ከፍተኛ ክብር አለው። ውትድርና ከሙያና ሥራ በላይ የነፃነትና የክብር መገለጫ፤ ሀገርን ከባዕድ ወረራ መከላከያ ጋሻ ነው ብሎ ያምናል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ህግና ሥርዓት አክባሪ በመሆኑ ለፓሊስም ከፍተኛ አክብሮት አለው። የፓሊስ ሥራ ወንጀልን መከላከልና ወንጀለኞችን ወደ ፍርድ ማቅረብ መሆኑ በኢትዮጵያ ባህል የተከበረ ቦታና እውቅና አለው።

በህወሓት የአገዛዝ ዘመን ግን ይህ እየተቀየረ ነው። የህወሓት አዛዦች እየመሩት ያለው የኢትዮጵያ ጦር ሠራዊት ሀገርን ከባዕድ ጠላት ከመከላከል ጋር ምንም ዝምድና በሌላቸው ሁለት አበይት ተግባራት ላይ ተጠምዷል። በህወሓት አዛዦች የሚመራው ሠራዊት ዋነኛ ተግባር ለሰብዓዊ መብቶቻቸው መከበር እና ለፍትህ መስፈን የሚታገሉ ዜጎችን ማጥቃት ሆኗል። የጦሩ ሁለተኛው አቢይ ተግባር ደግሞ ለአዛዦች የግል ጥቅም ማካበቻ ገቢዎችን በሚያስገኙ ሥራ ላይ መሠማራት ነው።

የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት ኢትዮጵያዊያንን ማጥቂያ ሠራዊት መሆኑ ሲቪሉን ሕዝብ ብቻ ሳይሆን የሠራዊቱንም አባላትን ጭምር ለህሊና ወቀሳ የዳረገ ጉዳይ ነው። ሆኖም ግን ይህ በህሊና ወቀሳ ብቻ ሊታለፍ የማይችል ወንጀል ነው። ሠራዊቱ በህወሓት እየታዘዘ የሚዘምተው በገዛ ራሱ ልጆች፣ እህቶች፣ ወንድሞችና ወላጆች፤ በገዛ ራሱ ጥቅሞች እና በገዛ ራሱ ላይ መሆኑ መገንዘብ ይኖርበታል። በገዛ ራሱ ጥቅሞች ላይ የሚዘምት አንድም ህሊና የሌለው አሊያም ነፃነት የተነፈገው ሰው ብቻ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ሠራዊቱ እየተራበና እየታረዘ አለቆቹ የታላላቅ ህንፃዎች ባለቤቶች፣ ባለፋብሪካዎች፣ የባንክና የኢንሹራንስ ኩባንያዎች ባለአክሲዮኖች የሚሆኑበት ሥርዓት ከዳር ሆኖ የሚመለከት መሆኑ የሚገርም ነው። ሠራዊቱ ቤተሰቦቹን መመገብ አቅቶት እያለ የአዛዦቹ ልጆች ለሽርሽር ዓለምን ይዞራሉ። እንዴት ነው ሠራዊቱ እየደኸየና እየሞተ አዛዦቹ እየከበሩ የሚሄዱት? ይህ አዋራጅ ሁኔታ እንዲያበቃ መታገል የሠራዊቱ ግንባር ቀደም ኃላፊነት ነው። ሠራዊቱ ወይ ባርነትን አሜን ብሎ መቀበል አለበት አለበዚያም እሱም እንደነሱ ሰው መሆኑን ማሳየት መቻል አለበት። በኢትዮጵያ ውስጥ የህወሓት አገዛዝ ወድቆ የሕዝብ ይሁንታ ያገኘ መንግሥት መመሥረቱ በከፍተኛ ሁኔታ ከሚጠቅማቸው የኅብረተብ ክፍሎች ግንባር ቀደሙ የመከላከያ ሠራዊት አባላት ናቸው። በዚህም ምክንያት የሠራዊቱ አባላት ለሥርዓቱ መውደቅ በግልጽም በስውርም መታገል የዜግነት ብቻ ሳይሆን አዕምሮ ያለው ሰው ሆነው በመፈጠራቸው የተቀበሉት ግዴታ ነው።

ፓሊስን በተመለከተም ሁኔታው ተመሳሳይ ነው። ህወሓት የኢትዮጵያን ሕዝብ አፍኖ ለመግዛት የቻለው በዋኛነት የፓሊስን ኃይል ለአፈናው ተግባር የሚጠቀም በመሆኑ ነው። የተቃውሞ ድምጾች በተሰሙ ቁጥር የኢትዮጵያ ፓሊስ በወገኖቹ ላይ የሚያወርደው ዱላ የሚዘገንን ሆኗል። ሰላማዊ ሰልፈኞችን በጥይት መግደልና ማቁሰል፤ አረጋዊያንን፣ ሴቶችንና ሕፃናትን መግደል፣ ማቁሰል፣ መደብደብ በዚህ ተግባር የተሠማሩ ፓሊሶችን በቡድንም በግልም በህግ የሚያስጠይቅ ከባድ ወንጀል ነው። በህወሃት እየተመራ ያለው የኢትዮጵያ ፓሊስ ተግባራት ተበዳዮችን ብቻ ሳይሆን ራሱ ፓሊስንም ጭምር አንገት የሚያስደፉ ተግባር ነው። ለመሆኑ አንድ ተራ የኢትዮጵያ ፓሊስ ባልደረባ ከህወሓት አገዛዝ ምን ተጠቀመ? መልሱ "ምንም" የሚል ነው። ይልቁንስ በህወሓት የአገዛዝ ዘመን ፓሊስ የተናቀና የተዋረደ ሥራ ሆነ። በህወሓት አገዛዝ ፓሊስ እንደሰለጠነ አዳኝ ውሻ "ያዝ" ሲሉት የሚነክስ፣ የሚያደማ፣ የሚቦጭቅ ሆኗል። ይህ ለፓሊስ፣ ወንጀልም ውርደትም ነው። በህወሓት አገዛዝ መገርሰስ እና በምትኩ የህግ የበላይነት የሰፈነበት ሥርዓት መስፈን ፓሊስ ከሁሉ በላይ ተጠቃሚ ነው፤ ሰብዓዊ ክብሩን ያረጋግጥለታልና።

ዛሬ በኢትዮጵያችን ውስጥ የታዘዙትን የሚፈጽሙ የጦርና የፓሊስ ሠራዊት አባላት ስላሉ ነው የህወሓት ሹማምንት ልባቸው ያበጠው። ለማስረጃ ያህል ሰሞኑን የህወሓቱ ሹም አባይ ፀሐዬ የአዲስ አበባ ዙሪያ ገበሬዎች በግዴታ መነሳታቸው የሚቃወሙትን ዜጎችን ሁሉ "ልክ እናስገባቸዋለን" ብሎ በሸንጎ የዛተው የታዘዘውን የሚፈጽም የጦርና የፓሊስ ሠራዊት መኖሩን ተማምኖ ነው። እስከ መቼ የኢትዮጵያ ጦር ሠራዊትና ፓሊስ ሕዝብን ማስፈራሪያ መሣሪያ ይሆናል?

አርበኞች ግንቦት 7: የአንድነትና ዲሞክራሲ ንቅናቄ የኢትዮጵያ የመከላከያና የፓሊስ ሠራዊት አባላት ለራሳቸው እና ለወገናቸው የሚበጀው ሥርዓት የቱ እንደሆነ ያውቃሉ ብሎ ያምናል። በዚህም ምክንያት ስብዕናቸውን እያዋረደ እና እያደኸያቸው ያለውን የህወሓት አገዛዝን ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር በመሆን ይፋለሙታል ብሎ ያምናል። ይህ ውሳኔ ግን ሠራዊቱ በጅምላ ሳይሆን እያንዳንዱ የሠራዊቱ አባል በግሉ የሚወስደው ውሳኔ እንደሆነ አርበኞች ግንቦት 7 ይገነዘባል።

በዚህም መሠረት ተደጋጋሚ ጥሪ እየተደረገለት፤ ጥሪውንም እየሰማ ከህወሓት ጋር ወግኖ ሕዝብን መውጋት የቀጠለ የሠራዊቱ አባል ላደረሰው ጥፋት በግል መጠየቁ የማይቀር መሆኑ ሊገነዘብ ይገባል። በእያንዳንዳንዱ የጦርና ፓሊስ ሠራዊት ባልደረባ ፊት የቀረበው ምርጫ "ለህወሓት ባርነት ታድራለህ ወይስ ራስህንና ሀገርን ነፃ ታወጣለህ" የሚል ነው።

ራስህንና ሀገርህን ነፃ ለማውጣት የመረጥክ የሠራዊቱና የፓሊስ ባልደረባ አሁኑኑ ሕዝባዊ ትግሉን ተቀላቀል። እስከዛሬ የበደልከውን ሕዝብ ለመካስ ምቹ ሁኔታ አለህ። በግልጽ የነፃነት ኃይሎችን እንድትቀላቀል፤ አሊያም አለህበት ሆነህ በውስጥ አርበኝነት እንድትደራጅና ተግባራዊ ሥራ እንድትጀምር መንገዱ ተመቻችቶልሃል።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

---

## ኢህአዴግ በደንብ አላገለገሉኝም ያላቸውን የመጅሊስ አመራሮችን አባረረ

ከሕዝበ ሙስሊሙ ፍላጎት ውጪ በ2005 ዓ.ም የተመረጡት የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት (መጅሊስ) አመራሮች የመንግስትን ፍላጎት ማርካት ባለመቻላቸውና በአመራሮቹ ላይ እምነት በመጥፋቱ በአስቸኳዋይ ስልጣናቸውን እንዲያስረክቡ በማድረግ በምትካቸው ሌሎች ተመርጠዋል። በአሁኑ ወቅት በሽብርተኝነት ወንጀል ተጠርጥረው በእስር ላይ የሚገኙት የሙስሊም መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላት ሼህ ኪያር መሐመድ ኢማንን ወደ ስልጣን ያመጣውን የመጅሊስ ምርጫ ሕገወጥ ነው በማለት እንዲታገድ ለከፍተኛው ፍ/ቤት ልደታ ምድብ ሰባተኛ ፍትሐ ብሄር ችሎት በወቅቱ ክስ አቅርበው የነበረ ቢሆንም ክሱ ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቶአል።

11 አባላት ያሉት የቀድሞ መጅሊስ አባላት ለኢህአዴግ የሚጠበቅባቸውን አገልግሎት አልሰጡም በሚል የሥራ አስፈጻሚ አባላትን በማስፈራራትና የኡላማዎች ም/ቤትን አንዳንድ ተለጣፊ የኢህአዴግ አባላትና ደጋፊዎችን በማስተባበር በፍጥነት ምርጫ እንዲካሄድ በተወሰነው መሰረት አስቸኳይ ጉባዔው ተካሂዷል። አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔውም ሐጂ መሀመድ አሚን ጀማልን ፤ ከኦሮሚያ ክልል፣ ፕሬዝዳንት አድርጎ የመረጠ ሲሆን የአማራ ክልሉ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክር ቤት ተወካይ ሼህ ዑመር ይማም የጠቅላይ ምክር ቤቱ ምክትል ፕሬዝዳንት፣ የአዲስ አበባው ተወካይ ሐጂ ከድር ሁሴን ዋና ፀሃፊ ሆነው እንዲሰሩ ተመርጠዋል። ጠቅላላ ጉባዔው ቀደም ሲል የነበሩትን አመራሮችን ሙሉ በሙሉ በማንሳት በአዲስ እንዲተኩ አድርጎአል።

የቀድሞ አመራሮች መጀመሪያውኑም የሕዝበ ሙስሊሙን ፍላጎት መሰረት አድርጎ በተካሄደ ነጻና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ወደሃላፊነት እንዳልመጡ የሚታወቅ ቢሆንም በእሁዱ ምርጫ ወቅት አመራሮቹ ከሃላፊነታቸው የተነሱት "የህዝበ ሙስሊሙን የልማት ጥያቄ አልመለሱም፣ አክራሪነትና ጽንፈኝነትን የመታገል ቁርጠኝነት አላሳዩም" በሚል መሆኑን የመንግስት መገናኛ ብዙሃን ዘግበዋል። ኢሳት አሁን የተሾሙት የመጅሊስ አመራር አባላት ከመንግስት የደህንነት ሃይሎች ጋር በጋራ እንደሚሰሩ የሚያሳይ ከስብሰባ ላይ በድብቅ የተቀረጸ ድምጽ መልቀቁ ይታወቃል። ገዢው ፓርቲ ሙስሊም ወጣቶችን እንዳዲስ በመያዝ እያሰረ መሆኑን የሚደርሱን መረጃዎች ያመለክታሉ። የፌደራል ሚኒስትር ዶ/ር ሽፈራው ተክለማርያም በቅርቡ በባህርዳር ባደረጉት የክልሎች የጸጥታ ግምገማ ላይ፣ መንግስት በመጅሊስ አመራሮች ላይ እርምጃ እንደሚወሰድ ፍንጭ ሰጥተው ነበር።

## በአዋሳ ከተማ አዲሱ ገበያ እየተባለ የሚጠራው ሰፈር

... ( ከገጽ 1 የዞረ )

ይህ በእንዲህ እንዳለ የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎ የሚገኙ የገበያ ቦታዎችን በእሳት በማውደም ቦታዎችን ለቅጥረኛ ባለሃብቶች በሊዝ በመቸብቸብ ዜጎችን ለችግር መዳረጉን በተለያዩ ጊዜያቶች መዘገባችን የሚታወስ ሲሆን ለአብነትም በቅርብ አመታት ውስጥ በአዲስ አበባ፤ በሃረርና በባህርዳር የደረሱት ከፍተኛ የእሳት አደጋዎች ተጠቃሾች ናቸው። በነዚሁ ከተሞች በእሳት አደጋዎቹ ጉዳት የደረሰባቸው ዜጎች ምንም አይነት ድጋፍ ከፋሺስታዊው አገዛዝ ሳይደረግላቸው፤ ቦታዎቻቸውን ተነጥቀው በችግር ህይወት እየማቀቁ እንደሚገኙ መዘገቡ አይዘነጋም።

---

# አሁንም ደግመን እንነግራችኋለን

ኢትዮጵያችን እግዚአብሔርንና ሰውን በማይፈሩ ጨካኞች እጅ ወድቃ የመከራ አገር ከሆነች ከሁለት አስርተ ዓመታት በላይ ተቆጥረዋል። በህዝባችን ላይ የተመዘዘው የመከራ ሰይፍም ወደ ሰገባው የሚመለስ አልሆነም። እንዲያውም በህዝባችን ላይ ሲዘንብ የቆየው የመከራ መንፈስ እንደገና ታድሶ ገና *"ልክ እናስገባችኋለን"* የሚል የጣዕረ ሞት ድምፅ ከህወሃት መንደር እየተሰማ ነው።

አባይ ፀሃይ የሚባለው ወላዋይና አደር ባይ ግለሰብ በህዝቡ ላይ ሲፈፅመው በኖረው ወንጀል ገና የረካ አይመስልም። ሌላ ግዲያ፤ ሌላ ስደት፤ ሌላ የላቀ መከራ ለኢትዮጵያዊያን ደግሶላቸዋል። አባይ ፀሃይ ለአዲስ አበባ ከተማ ልቀት እርሱ ብቻ አሳቢ፤ እርሱ ብቻ ተቆርቋሪ ሁኖ ራሱን ሹሟል።የአዲስ አበባም ሆነ በአካባቢው የሚኖረው ኗሪ ህዝብ ግን አባይ ፀሃይን የሚያውቁት በእኩይ ተግባሩ እንጂ በደግ ተግባሩ እንዳለሆነ እኛ ልናስታውሰው እንወዳለን። በዚህ ግለሰብ አማካሪነት የተጀመረው ኗሪውን ህዝብ የማፈናቀል፤ ቤተሰብን የመበተን፤ የህዝቡን አብሮነት የማፍረስ ተግባር ገና ተጠናክሮ እንደሚቀጥል "ገና ልክ እናስገባችኋለን" በሚል መፈክር ሥር እንደሚቀጥል ታቅዷል። አዲስ አበባን በማስፋፋት ሰበብ ብዙ ገበሬዎች ከኖሩበት መንደር ያለምንም ካሳ ተፈናቅለው የሌላ ሎሌ እንዲሆኑ መደረጉ የሚረሳ አይደለም። ይሄን የአንድን ህዝብ ማንነት የማጥፋት ድርጊትን የተቃወሙ ብዙ ወጣቶች በሞት እና በእሥራት እንደተቀጡም አረሳነውም። ትላንት የፈሰሰው ደም ሳይደርቅ፤ የፈሰሰው እንባ ሳይታበስ፤የተበተነው ሳይሰበሰብ፤ የተሰበረው ሳይጠገን እንደገና ለሌላ ዙር ጥፋት እየተዘጋጁ እንደሆነ ነግረውናል።

አባይ ፀሃይ "ልክ እናስገባችኋለን" ሲል የተማመነው ጠመንጃ ያነገተውን ኢትዮጵያዊ ወታደር እንጂ ህዝብን እንዳልሆነ እናውቃለን። ወታደር አገሩን መጠበቅ፤ ህዝቡንም ከጥፋት መታደግ፤ አጠቃላይ የአገሪቷን ህግም ማስከበር ዋናው ተልዕኮው ነበር። የአገራችን ወታደሮች ግን ዋናውን ተልእኳቸውን ትተው ኢትዮጵያን እንደ አገር እንዳትቀጥል የሚያደርጉ ቡድኖችን እድሜያቸውን ለማራዘም እየሰሩ እንደሆነ እያየን ነው።በአገራችን ጠመንጃ የታጠቁ ኃይሎች መከላከያ ኃይል አባላት፤ የፖሊስ አባላት፤ የፌዴራል ፖሊስ አባላት እና በአገራችን ታሪክ በነፍሰ ገዳይነቱ የሚታወቀው አግዓዚ የተባለው ክፍለ ጦር አባላት እና የአገር ውስጥ ደህንነት አባላት የህወሃትን ዕድሜ ለማራዘም ከልብ የመነጨ ፍላጎት አላቸው ብለን አናምንም። እነዚህ ኃይሎች የወጡበትን ጎጆ፤ ነገ ዞሮ መግቢያ የሚሆናቸውን ማህበረሰብ ወደውና ፈቅደው ያፈርሳሉ ብለን ለማሰብ ይቸግረናል።በሌላ በኩል ደግሞ ድርጊታቸው ብዙዎችን እያስከፋ እንደሆነም እናውቃለን።

አሁንም ደግመን ደጋግመን በኢትዮጵያችን ጠመንጃ ላነገቱ ኃይሎች መልዕክት መላካችንን አናቋርጥም። ጠመንጃውን ያነገቱ ኃይሎች ካነገቱት ጠመንጃ የተለዩ ናቸው። እነዚህ ኃይሎች ስሜት አሏቸው፤ ፍላጎት አሏቸው፤ ማሰብ የሚችል አዕምሮም እንዳሏቸውም የሚካድ አይደለም።የሚያዝንና የሚደሰት ስሜት፤ ለመኖር ፍላጎት፤ በጎውን ከክፉ ለመለየት የሚያስችል አዕምሮ ያሏቸው ስለሆነ ፈፅሞ እስከ ሚመሽ ድረስ መልዕክታችንን ከመስደድ አናቆምም። መልዕክታችንም አጭርና ግልፅ ነው። በዚያች አገር ውስጥ ጠመንጃ የታጠቀው ኃይል ጋር ጠላትነት የለንም።በእኛ እምነት መከላከያ ኃይል፤ ፖሊስ እና የደህንነት ሠራተኞች ጠላቶቻችን አይደሉም። እኛ ጠላት የምንለው ጠመንጃ የታጠቀውን ድሃ እና ከርታታ ኢትዮጵያዊ ሳይሆን ይህን ኃይል በገዛ ወገኑ ላይ ሰይፉን እንዲመዝ እና የንፁሃንን ደም እንዲያፈስ የሚያደርገውን ኃይል ነው።የአገሪቷ መከላከያ ኃይል አሁን ባለበት ሁኔታ ለተሻለ ውጤት የሚያበቃው አማራጭ ስለሌለው ሂሊናው እየወቀሰውም ቢሆን የገዛ ወገኑን ደም እያፈሰሰ ለመቆየት የተገደደ ይመስላል። ይህን ማለታችን የድርጊቱን መፈፀም ትክክል ነው እያልን አይደለም። በማንኛውም መለኪያ የንፁህ ሰውን ደም ማፍሰስ ትክክል አይደለም። በሰማይ በእግዚአብሄር ፊት የሚያስጠይቅ፤ በምድር በሰው ዘንድም የሚያስወቅስ ክፉ ተግባር መሆኑን ሳንናገር አናልፍም።

እስከ ዛሬ የተሻለ መረጃ ስለሌለኝ፤ የተሻለ አማራጭ ስላጣሁ፤ የተሻለን መንገድ ለመፈለግ ሁኔታው ስላልፈቀደልኝ ከሂሊናየ ውጪ ሁኜ ለመኖር ተገድጃለሁ የሚለው ምክንያት አሁን አብቅቷል። አሁን መረጃ አለ፤ ኢትዮጵያን እንደ አገር እንድትቀጥል ለማስቻል የተሻለ አማራጭም አሁን ተዘጋጅቷል። መረጃና አማራጭ መንገድ ካለ ደግሞ ከሂሊና ጋር ታርቆ እንደ ሰው ለመኖር ሁኔታው የተመቻቸ ሁኗል።

የኢትዮጵያ መከላከያ ኃይል፤ የፖሊስ ሠራዊት አባላት፤የአገር ውስጥ የደህንነት ኃይሎች ሆይ ስሙን !

ህወሃቶች እናንተን ተገን አድርገው የገዛ ወገኖቻችሁን "ልክ እናስገባለን" ማለታቸውን ሰምታችኋል የሚል ግምት አለን። ልክ ማስገባት ማለት-ከሥራ ማባረር፤ ከትውልድ ሥፍራ ማፈናቀል፤ እስር ቤት መጨመር፤ ለስደት መዳረግ እና መግደል ማለት ነው። የአባይ ፀሃይ ልክ ማስገባት ይሄን ይመስላል። ይሄን የምትፈፅሙት ደግሞ ጠመንጃ ያነገታችሁ ኃይሎች ትሆናላችሁ። ወገኖቻችሁ በህወሃቶች እጅ እንባቸውን በመዳፋቸው ሲያፍሱ ኑረዋል።በህወሃት አገዛዝ ሥር ያለች አገራችሁ ከውዳቂ አገራት ተርታ ገብታለች፤ ከዓለም አስር ፍፁም ድሃ አገሮች መካከል አንዷ ሁናለች።የአገራችሁ ወጣቶች ሞትን ፊት ለፊታቸው እያዩ ተሰደው የዓዞና የበርሃ ዕራት ሁነው ቀርተዋል። ከዚህ የተረፉትም የዓረብ መጫወቻ ሁነዋል። ይህ ሁሉ መከራ ህወሃት በተባለው ክፉ ዘረኛና ቂመኛ ቡድን ይፈፀማል። አሁን ይሄን በቃ ለማለት ግዜው ነው። ከእንግዲህ ወዲያ ታዝዤ ነው፤ ለእንጀራ ብየ ነው፤ ልጆቼን ላሳድግ ብየ ነው፤ አማራጭ አጥቼ ነው፤ የሚሉ ምክንያቶች ሚዛን የሚያነሱ ባለመሆናቸው ተቀባይነት የላቸውም።

አሁን አስተማማኝ አማራጭ አለ። የኢትዮጵያ ውረደት ያንገበገበን፤ የህዝባችን ጉስቁልና ያስቆጨን ወገኖች የአያቶቻችንን ጋሻና ጦር አንስተን ለግዳጅ ተዘጋጅተናል። ከመቸውም ግዜ በተሻለ ህዝባዊ መሠረት ላይ የቆመ ድርጅት መሥርተን ንቅናቄ ጀምረናል። ትግላችን ኢትዮጵያዊያን ከተዘፈቁበት ጭለማ ወደ ብርሃን የሚያሻግር ነው። ትግላችን ህወሃት የጫነውን የዘረኝነት ቀንበር የሚሰብር ነው። ትግላችን ህወሃት የዘረጋውን የዝርፊያ መረብ የሚበጣጥስ ነው። ትግላችን ህዝቡን በሙሉ የተጫኑ ጥቂት መንደርተኞች ሥፍራቸውን እንዲይዙ ማድረግ ነው።ትግላችን ጎጠኛ አስተሳሰብን አምክኖ ብሄራዊ ስሜትንና ውህደትን የሚፈጥር ነው። ትግላችን ዜጎች በዜግነታቸው ብቻ በኢትዮጵያ ውስጥ በማንኛውም ሥፍራ ያለ ፍርሃት የሚኖሩበትን ሁኔታ የሚፈጥር ነው። ትግላችን አብዛኛው ህዝብ በመረጠው መንግስት የሚተዳደርበት፤ ይህም መንግስት ህዝቡን ፈርቶና አክብሮ የሚሠራበት ሁኔታ የሚፈጥር ነው። ትግላችን የአገሪቷ መከላከያ ኃይል አገሩንና ህዝቡን የሚጠብቅ እንጂ የገዛ ወገኑን ደም በከንቱ የሚያፈስበት ሁኔታ እንዲያበቃ የሚያደርግ ነው።ጠመንጃውን ያንገትከው ኃይል የቀረበልህ አማራጭ መሥመር ይሄ ነው።

ደግመን እንነግርሃለን አሁን አማራጭ መንገድ አለህ። በገዛ ወገኖችህ ላይ ሰይፍህን ለመምዘዝ እምቢ የማትል ከሆነና አሁንም በዚያው በጭለማ መንገድ መሄድን ከመርጥክ መጨረሻህ መልካም አይሆንም። እኛ እንድሆንን ተነስተናል። ከመንገዳችን የሚያቆመን ምዳራዊ ኃይል አይኖርም።የቃየል ልጆች ሲያጠፉን እንዲያው ዝም ብለን የምንጠፋ አይደለንም።ከእኛ ዘንድ እውነት አለ፤ ከእኛ ዘንድ የነፃነት ብርሃን አለ፤ ከእኛ ዘንድ የፍትህ ዘንግ አለ፤ከእኛ ዘንድ የእኩልነት ሚዛን አለ፤ ከእኛ ዘንድ እግዚአብሄር አለ።ይሄን ሁሉ ይዘን እናሸንፋለን እንጂ አንሸነፍም።የምናሸንፈው ለበቀል እንዳይደለ አሁንም እንነግራችኋለን። የምናሸንፈው በክፉው ላይ መልካሙን ዘር በመዝራት ነው።በጭቆና ላይ ነፃነትን፤ በአድልዎ ላይ ፍትህን፤ በህግ አልባነት ላይ የህግ የበላይነትን፤ በጎጠኛ አስተሳሰብ ላይ ብሄራዊ አስተሳሰብን ማስረፅ ስንችል ነው አሸንፈናል የምንለው። የጎሰኛነትን አጥር አፍርሰን የኢትዮጵያዊነት ስሜት ማስረፅ ስንችል ነው አሸንፈናል የምንለው። እኛ ስናሸነፍ የሚሆነው ይሄው ነው። ከእኛ ዘንድ የበቀል ስሜት የለም። ከእኛ ዘንድ ያለው ሁሉም ከህግ በታች ሁኖ ህግና ፍትህ እንዲነግሱ የሚያስችል ብርቱ ፍላጎት ነው።

ስለዚህ ጠመንጃ ያነገታችሁ ኃይሎች እኛ ከቆምንለት ቅዱስ ዓላማ ጋር እንድትተባበሩ እንጠራችኋለን።ኑና የጭለማ ኃይሎችን ምሽግ አፍርሰን የብርሃን ልጆችን አምባ አብረን እንሥራ። ኑና አብረን የወገኖቻችንን እምባ እናብስ። ኑና በግፍ ያለፍርድ የታሠሩትን እናስፈታ ።ኑና የጭቆናን ቀንበር አብረን እንስበር። ኑና አብረን አገራችንን ከፍ ከፍ እናድርጋት።

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !!

........................................................................................................................................................

## ጠቅላይ ሚኒስትር ሀይለማርያም ደሳለኝ የወልቃይትን ህዝብ ለማነጋገር ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀሩ

የህወሀትን 40ኛ ዓመት አክብረው ሲመለሱ እግረ መንገዳቸውን በአማራ ክልል የተለያዩ አካባቢዎችን እየጎበኙ ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ሀይለማርያም ደሳለኝ፤ የካቲተ 16 ቀን በወልቃይት ሊያደርጉት የነበረውን ጉብኝት የህዝቡን ተቃውሞ በመፍራት መሰረዛቸው ነዋሪውን ክፉኛ አስቆጥቷል።የወልቃይት ነዋሪዎች ለኢሳት እንደገለጹት ጠቅላይ ሚኒስትሩ የካቲት 16 ቀን ወልቃይትን እንዲጎበኙ በአካባቢው ሹመኞች መነገሩን ተከትሎ በየገጠር የሚኖረው ህዝብ ሳይቀር በመሰባሰብ እና ምሳ በማሰናዳት ሲጠባበቃቸው ቢውልም የውሀ ሽታ ሆነው ቀርተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩን በአካል አግኝቶ የአስተዳደራዊ በደል ጥያቄውን ለማቅረብ ከ8 ሺህ በላይ ህዝብ ተሰባስቦ እንደነበር የገለጹት የነዋሪዎቹ አስተባባሪዎች፤ ህዝቡ ተቃውሞውን ለመግለጽና ጥያቄ ለማቅረብ እንደተዘጋጀ የተረዱት የአካባቢው ሹመኞች ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወደ ወልቃይት እንዳይገቡ አድርገው ቅጠታ ወደ ደጀና እንደወሰዷቸው ተናግረዋል። ይህ በመሆኑም ተሰባስቦ ሲጠባበቅ የነበረው ህዝብ በቁጣና በብስጭት ወደ ቤቱ መመለሱን የገለጹት አስተባባሪዎቹ፤ ንዴታቸውን መቆጣጠር የተሳናቸው የአካባቢው ወጣቶችም በአደባባይ የህወሀትን ባንዲራ በማቃጠል የዚያኑ እለት ለትግል ወደ በረሀ መውጣታቸውን ተናግረዋል። ቀርቦ በማናገር እንጂ ከህዝብ በመደበቅ ወይም በመሸሽ ከችግር መሸሽ እንደማይቻል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሊረዱት ይገባል ያሉት ነዋሪዎቹ፤ አንድ የሀገር መሪ- ከህዝብ ጋር የዚህ ዓይነት ድብብቆሽ ጨዋታ ውስጥ መግባቱ እጅግ እንዳሳፈራቸውም ገልጸዋል።

"አማራዎች ሆነን ሳለን ያለፍላጎታችን ወደ ትግራይ ክልል እንድንጠቃለል ተገደናል፣ የማንነት ጥያቄያችን ምላሽ እንዲያገኝ ጥያቄ በማቅረባችን ለበርካታ ዓመታት ተነግረው የማያለቁ በደሎችና ግፎች እየተፈጸሙብን ነው" የሚሉት ወልቃይቶች፤ "በቅርቡ በተደረጀ ሁኔታ በደብዳቤ ላቀረብነው አቤቱታም እስካሁን ከመንግስት ምላሽ አላገኘንም፤ መንግስት መልስ የማይሰጠን ከሆነ፤ ራሳችን መልስ ለመስጠት እንገደዳለን" በማለት አስጠንቅቀዋል። ይህ በእንዲህ እንዳለ የወልቃይት ህዝብ ላለማየት ተራምደውት ያለፉት አቶ ሀይለማርያም ትናንት ምሽት ከ አቶ አርከበ እቁባይና ከአማራ ክልል ርእሰ-መስተዳድር ከ አቶ ገዱ አንዳርጋቸው ጋር በመሆን ኮምቦልቻ ከተማ መግባታቸው ታውቋል። ዛሬ ጧት የኮምቦልቻ ከተማ ተማሪዎች ለአቶ ሀይለማርያም አቀባበል ለማድረግ በሚል ከትምህርት ገበታቸው በግዳጅ መወሰዳቸውን የገለጹት ምንጮችን የከተማውም ነዋሪ በተመሳሳይ መንገድ ለ አቀባበል ተብሎ በግዳጅ እንዲወጣ መደረጉን ጠቁመዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ማለዳ ላይ የዛሬ ዓመት የተመረቀውን የ ኮምቦልቻ አውሮፕላን ማረፊያ እንደ አዲስ እንዲመርቁ ከተደረገ በሁዋላ ለአዋሽ-ኮምቦልቻ የባቡር ሀዲድ ግንባታ የመሰረት ድንጋይ ማስቀመጣቸውን የገለጹት ምንጮች፤ የመሰረት ድንጋይ የማኖር ፕሮግራሙ የተካሄደውም የሸህ መሀመድ ሁሴን አል አሙዲ የቆርቆሮ ፋብሪካ አጠገብ በተጣለ ዳስ ውስጥ እንደነበር አመልክተዋል።

ወደ ዳሱ እንዲገቡ የታደሙት "አዋሽ -ኮምቦልቻ ሀገ ገበያ" የሚል መግቢያ ባጅ የተሰጣቸው የኢህአዴግ ካድሬዎች ብቻ መሆናቸውን የጠቀሱት ምንጮች፤ ይሁንና ከነበረው እጅግ ጥብቅ ፍተሻ አኳያ፤ ተጋባዦቹ የኢህአዴግ አባላት ሳይሆን አደገኛ ጠላት ነበር የሚመስሉት ብለዋል። አቶ ሀይለማርያም የመሰረት ድንጋይ ማስቀመጣቸውን ተከትሎ "ኢህአዴግን ምረጡ" የሚል ቅስቀሳ መደረጉን የጠቀሱት ምንጮች፤ የመሰረት ድንጋይ ሊጥሉ መጡ የተባለውም ሆነ ከአመት በፊት የተመረቀን አውሮፕላን ማረፊያ እንደ አዲስ እንዲመርቁ የተደረገውምለምርጫው ህዝቡን ለማታለል እንደሆነ በደንብ ገብቶናል"ብለዋል። የምንልሰውና የምንቀምሰው ባጣንበት ወቅት በባቡር ፕሮፖጋንዳ ሊያታልሉን አይችሉም ያሉት ነዋሪዎቹ፤ በትራንስፖርትም ረገድ ቀደም ሲል 1 ብር የነበረው የታክሲ ታሪፍ እስከ 3 ብር፣ 2 ብር የነበረው እስከ 6 ብር ደርሶ ህዝቡ እየተማረረ እንደሚገኝ አመልክተዋል።

### የአለም ባንክ በኢትዮጵያ የተፈጸሙትን የሰብአዊ መብት ጥሰቶች በጽሞና እንዲያቸው ተጠየቀ

አለማቀፉ የሰብአዊ መብት ድርጅት ሂውማን ራይትስ ወች ባወጣው አስቸኳይ መግለጫ በአለም ባንክ ድጋፍ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች፣ የባንኩን ፖሊሲ የሚጻረሩ ሆነው መገኘታቸውን የአለም ባንክ የውስጥ የምርመራ ክፍል ማሳወቁን ገልጿል። ይሁን እንጅ የባንኩ ማኔጅመንት በባንኩ የውስጥ የምርመራ ቡድን የቀረበውን ሪፖርት የሚቃረንና ባንኩን ከተጠያቂነት የሚያድን ሌላ ሪፖርት አቅርቧል። የአለም ባንክ የዳይሬክተሮች ቦርድ በምርመራ ክፍሉና በማኔጅመንቱ የቀረቡትን ሁለት የተለያዩ አስተያየቶችን ለማየት ከሶስት ቀናት በሁዋላ ይሰበሰባል።

የምርመራ ክፍሉ፣ ከጋምቤላ አካባቢ የተፈናቀሉ ሰዎች ያቀረቡትን አቤቱታ ተንተርሶ ምርመራ ያካሄደ ሲሆን፣ በምርመራውን የአለም ባንክ ራሱ ያወጣውን ፖሊሲ መጣሱን አረጋግጧል። በሂውማን ራይትስ ወች አለማቀፍ የገንዘብ ተቋማትን አስመልክቶ ምርምር የሚያደረጉት ጄሲካ ኢቫንስ እንደተናገሩት፣ የአለም ባንክ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶች ለሰብአዊ መብት ጥሰቶችን ተገቢውን ቢታ አልሰጠም። ተመራማሪዋ፣ ባንኩ በኢትዮጵያ ላይ የሚያከናውነውን ፕሮግራም መቀየር፣ በዚሁ ፕሮግራም ለተጎዱት ችግረኞች መፍትሄ መስጠት ሲችል ያንን አላደረገም ብለዋል። በሰፈረ ፕሮግራም በርካታ ዜጎች ለችግር መዳረጋቸውንና መንግስት ያከናወነው ሰፈራ ፕሮግራም ከአለም ባንክ ፕሮጀክት ጋር በቀጥታ የሚገናኝ መሆኑ በመግለጫው ተጠቅሷል። በባንኩ የምርመራ ቡድን የቀረቡትን ችግሮችና የመፍትሄ ሃሳቦችን ተግባራዊ እንደማድረግ፣ የባንኩ ማኔጅመንት በተቃራኒው አሁን የሚታየውን ችግር የሚያጠናክር ሌላ የድርጊት መርሃ ግብር ነድፏል ሲል ሂውማን ራይትስ ወች ገልጿል።

የምርመራ ቡድኑ፣ የኢትዮጵያ መንግስት በሰብአዊ መብት ዙሪያ ላይ የሚሰሩ የሲቪል ሶሳይቲ ተቋማትን ለመቆጣጠር የወጣው ህግ እንዲሻሻል አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን አለመውሰዱ በመግለጫው ጠቅሷል። የአለም ባንክ የዳይሬክተሮች ቦርድ የማኔጅመንቱን መልስና አዲስ የወጣውን የድርጊት መርሃ ግብር በመመለስ፣ የምርመራ ቡድኑ ባነሳቸው ጉዳዮች ላይ ትኩረት እንዲያደርግ ሂውማን ራይትስ ወች ጠይቋል።

ለትክክለኛ ልማት እንቅፋት የሆነው የሰብአዊ መብት ጉዳይ ትኩረት ያገኝ ዘንድ በባንኩና በኢትዮጵያ መንግስት ከፍተኛ ባለስልጣናት መካከል ውይይት ሊካሄድ እንደሚገባውም የሰብአዊ መብት ድርጅቱ ጠይቋል። ሊጋሽ አገራት በኢትዮጵያ የሚታዩ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን ግምት ውስጥ እንደማይከቱ የሚያመለክተው መግለጫው፣ በፕሮጀክቶች የድሆችን ተሳትፎ እንዲሁም ከሚለገሰው ገንዘብም ተጠቃሚ የሚሆኑበት ፕሮግራም መነደፍ እንዳለበት ድርጅቱ አስታውቋል።

### አብዛኞቹ የመንግሰት ጋዜጠኞች የኢህአዴግ አባላት መሆናቸውን … ( ከገጽ 1 የዞረ )

ማስረጃ እንደሌለ አስተያየታቸውን የሰጡን አንድ የሚዲያ ባለሙያ ተናግረዋል። ጋዜጠኞች የኢህአዴግ አባላት የሚሆኑት ጥቅማቸውን አስበው እንጅ በድርጅቱ አምነውበት ላይሆን እንደሚችል፣ ከሚሰሩት ስራ መናገር ይቻላል የሚሉት አስተያየት ሰጪው፣ አብዛኞቹ አጋጣሚውን ሲያገኙ ወደ ውጭ ወጥተው መቅረታቸው አባልነቱ ለጥቅም መሆኑን ያረጋግጣል ብለዋል። በሌላ ዜና ደግሞ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ህዳሴ የሚባለውን የኢህአዴግ አዲስ ልሳን ስፖንሰር እንዲያደርጉ እየታዘዙ ነው።

ኢሳት ከአዲስ አበባ ኢህአዴግ ኮሚቴ ጽ/ቤት በአስተዳደርና ፋይናንስ መምሪያ ኃላፊ ወ/ሮ ቅድስት ወ/ጊዮርጊስ ተፈርሞ በወጣ ደብዳቤ ላይ ለማረጋገጥ እንደቻለው፣ በሁለት ሳምንት አንድ ጊዜ ታትሞ የሚወጣው ህዳሴ የተሰኘው የኢህአዴግ የፖለቲካ ልሳን ጋዜጣ በስፖንሰር ሺፕ ሰበብ በመንግስት መ/ቤቶች ባጀት ወጪ እንዲታተም እየተደረገ ነው። ከጽ/ቤቱ የካቲት 5 ቀን 2007 ዓ.ም ከ5 በላይ ለሚሆኑ የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር መ/ቤቶች በአድራሻቸው ተጽፎ የተሰራጨው ደብዳቤ እንደሚያመለክተው እያንዳንዱ መ/ቤት ስፖንሰር ለማድረግ የተስማማበትን በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አንድነት ቅርንጫፍ በአዲስ አበባ ኢህአዴግ ኮሚቴ ጽ/ቤት ስም ወደሚታወቀው ባንክ አካውንት ገቢ እንዲያደርጉ የሚያሳስብ ሲሆን ለአንድ ጊዜ ማሳተሚያ እስከ 300,000 ብር እንዲከፍሉ ታዘውዋል።


### የአርበኞች ግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz

<u>አጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz

**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**

**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።



ውድ አንባቢዎቻችን

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዣችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## የግንቦት 7ና የአርበኞች ግንባር መዋሃድ በፋሽስቱ ወያኔ መንደር

... ( ከገጽ 1 የዞረ )

በሌላ ዜና የግንቦት 7 ንቅናቄና አርበኞች ግንባር ተዋህደው በፈጠሩት የፈረጠመ ወታደራዊ ጡንቻ የተርበደበደው የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ ከሰሞኑ የተለመደ የፈጠራ ድራማውን ለመልቀቅ ዝግጅት በማጠናቀቅ ላይ መሆኑ ታውቋል። የፈጠራ ድራማው በዋናነት በወታደራዊ ሐይሉ ላይ ያነጣጠረ መሆኑን ያደረሱን የውስጥ ምንጮቻችን የአርበኞች ግንቦት 7 የሰራዊት አባላት የነበሩና የከዱ ናቸው የተባሉ 16 የወያኔ ቅጥረኞች እንደሚተውኑበት ለማወቅ ችለናል። ለ16ቱ ተዋንያኖች የአርኞች ግንቦት 7 ት ወታደራዊ ልብስ ተዘጋጅቶላቸው ቀረፃው መካሄዱን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን በድራማው ግለሰቦቹ በአፋር በኩል ድንበር አቋርጠው የገቡ በማስመሰል ፊልሙ መዘጋጀቱ ታውቋል።

## በወልቃይት ጠገዴ አንዣቦ የሚገኘው ህዝባዊ አመጽ

... ( ከገጽ 1 የዞረ )

ይህ በእንዲህ እንዳለ ከሰሞኑ በወረዳዎቹና በየገጠር ቀበሌዎች እየተቀሰቀሰ የሚገኘው የህዝብ ብሶትና አመጽ ያሰጋቸው የዘረኛው ህወሓት ቱባ ሹማምንት ከነዋሪዎች ጋር እንዲመክር በሚል አሻንጉሊቱ ሃይለማርያም ደሳለኝን ወደ ወልቃይት ልከው የነበረ ቢሆንም ተላላኪው ሃይለማርያም በተዘጋጀው ህዝባዊ የውይይት መድረክ ላይ ከህዝቡ ለቀረበለት አቤቱታ መልስ መስጠት ተስኖት ተዋርዶና ተሸማቆ አንገት መድፋቱ ታውቋል። ህዝባዊ ወይይቱ በተቃውሞ ተናውጦ መበተኑንም የደረሰን መረጃ ያሳያል። በዘረኛው የህወሃት አገዛዝ በደረሰባቸው ከፍተኛ በደል ክፉኛ የተቆጡት ቁጥራቸው ከ 7 ሺ በላይ የሚጠጉ አርሶ አደሮች ለጥያቄዎቻቸው መልስ ይሰጠን በማለት ቅጥረኛው ሃይለማርያም ደሳለኝ ምሳ ለመብላት ወደ ተዘጋጀት ቦታ ሲያመራ በሰልፍ ሆነው የተከተሉት ሲሆን የአርሶ አደሮችን ቁጣ የተመለከቱት የአገዛዙ ቅጥረኛ ሹማምንት አሻንጉሊቱ ሃይለማርያም ምሳ ሳይበላ አምልጦ ከአካባቢው እንዲወጣ ማድረጋቸው ታውቋል።

## አባይ ፀሀዬ የአዲስ አበባን ማስተር ፕላን በኃይል እንተገብራለን ብሎ መዛቱ ... ( ከገጽ 1 የዞረ )

ባለፈው አመት ሚያዚያ ወር ላይ የጉጅሌው ወያኔ አጋዚ ጦር በወሰዱት የሐይል እርምጃ ከ 70 በላይ የኦሮሞ ተወላጆች በጥይት ተደብድበው መገደላቸውና በሺዎች የሚቆጠሩ መታሰራቸውን ያስታወሰው መግለጫው፣ የዘረኛው ህወሃት አገዛዝ ባለፉት 24 አመታት በኦጋዴን፣ ጋምቤላ፣ ሲዳማና በሌሎች ኢትዮጵያውያን ላይ የፈጸማቸው ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ሆን ተብሎ ታቅዶ የተፈጸሙ ናቸው ብሏል።

የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ በንፁሃን ዜጎች ላይ እየፈጸማቸው ባለው አረመኔያዊ ጭፍጨፋዎች በዘር ማጥፋት ወንጀል እንደሚያስጠይቀው የሰብአዊ መብት ሊጉ አክሎ ገልጿል። የጉጅሌው ቁልቁላ አባይ ጸሃየ የአዲስ አበባ ማስተር ፕላንን በሚቃወሙ ላይ ሁሉ፣ የኦህዴድ ሹማምንትን ጨምሮ፤ የሃይል እርምጃ እንደሚወሰድባቸው ዝተዋል።

## የወያኔ ፋሽስቶች ወያኔ የተማረውን ኢትዮጵያዊ በፍጹም እንደማያምኑ ... ( ከገጽ 1 የዞረ )

የቡድን ሰራተኞችን የያዘው አራተኛው ክፍል፣ በስሩ ስለሚካተቱ ሰዎች አይዘረዝርም። 1 ለ5 ሰራተኞች የተባለው ደግሞ የመጨረሻው የአደረጃጀቱ ክፍሎች እና ታች ያለውን የመንግስት ሰራተኛ የሚመለከተው ነው። የለውጥ ሰራዊቱ በዚህ መልኩ ተዋቅሮ እንደሚጓዝ ሰነዱ አስምሮበታል።ኢህአዴግ የመንግስት ሰራተኛውን በራሱ መንገድ ለመቅረጽ የተጠቀመባቸው መንገዶች ሁሉ የተፈለገውን ውጤት እንዳላስገኙለት በሰነዱ ላይ ጠቅሶ፣ ቀጣዩ ስራ የለውጥ ሰራዊቱን በዚህ መልኩ አደራጅቶ መጓዝ መሆኑንም አስቀምጧል።የመንግስት ሰራተኛው ስለ አገሪቱ ህገ መንግስት፣ ስለ ህዝቦች ትግልና አገራዊ ህዳሴ እንዲሁም የልማታዊ ዲሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ትግልና ፈተናዎች በቂ ግንዛቤ ካልያዘና ይህንንም በተጨባጭ በተግባር ማሳየት ካልቻለ ፣ ሚናውን ተወጥቷል ብሎ መናገር እንደማይቻል ሰነዱ ይጠቃሳል።

የተማሩት የአገዛዙ የተቋማት ሰራተኞች "ፋሺስቱ ወያኔ ቢቀየር የአገዛዙ ህልውና ቢንኮታኮት ግድ" እንደማይሰጣቸው ሰነዱ ይጠቅስና፣ በምርጫ ድምጽ አሰጣጥም መርጦ ካልወጣ በስተቀር የማይታመን፣ በተጠራበት ሰልፍ የሚገኝ ነው" ሲል ፋሺስታዊው አገዛዝ ለሰፊው የኢትዮጵያ ጭቁን የሰራተኞች መደብ ያለውን ጥላቻ አስቀምጧል። በመጨረሻም የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ የተማረውን ሰራተኛ ክፍል በራሱ መንገድ ለመቅረጽ የተጠቀመባቸው መንገዶች ሁሉ ሙሉ በሙሉ መክሸፋቸውንና የተፈለገውን ውጤት እንዳላስገኙለት በሰነዱ ላይ ተጠቅሷል።